# 2ኛ ጢሞቲዎስ ጥናት (38)

## ጥናት አንድ 2ኛ ጢሞ 1፡1-18

የጥናት ዓላማ፡- በዙሪያችን ያሉት ሁሉ በነበሩበት ባናገኛቸው እንኳን፤ እንደ ጳውሎስ የጌታን ታማኝነት ተመልክተን በአላማችን ወደፊት መግፋትና ሌሎችም እንዲገፉበት ማበረታታት እንደሚኖርብን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹መከራን የምቀበለው ለዚሁ ነው፤ ሆኖም ያመንኩትን እርሱን ስለማውቅ አላፍርበትም፤ የሰጠሁትንም ዐደራ እስከዚያች ቀን ድረስ መጠበቅ እንደሚችል ተረድቻለሁ፡፡›› 2 ጢሞ 1፡12

1. 2ኛ ጢሞ 1፡1-18 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ1-2 ላይ ጸሐፊው ራሱን ምን በማለት ነው የሚያስተዋውቀው? ጢሞቲዎስንስ ምን በማለት ያስተዋውቃል?
2. በቁ3 ላይ ጳውሎስ ለጢሞቲዎስ ምን ሲያደርግ ነው የምንመለከተው? በቁ6 ላይስ ሐዋርያው በእምነት ልጁ ለሆነው ለጢሞቲዎስ ምን ሲያደርግ ይታያል? ከዚህ የጳውሎስ አደራረግ መማር የምትችለው ምን ነገር አለ?
3. ከቁ3-5 ያሉትን ቁጥሮች በማንበብ በጢሞቲዎስ ህይወት የሚንጸባረቀው የእምነት ዓይነት ምን ይመስላል? በጢሞቲዎስ ውስጥ ከሚታየው የእምነት ዓይነት የተለየ እምነት ሊኖር ይችላል ማለት ነው ወይ? አስረዳ፡፡ ለምን ይመስልሃል ጳውሎስ የጢሞቲዎስን እናትና አያት በዚህ ሥፍራ መጥቀስ የፈለገው?
4. በቁ6-7 ላይ ጢሞቲዎስ ስለተቀበለው ስጦታ አስመልክቶ የምታያቸውን ቢያንስ ሶስት ሃሳቦችን ተናገር፡፡ ቅዱሳን ከእግዚአብሄር እንደተቀበልን የሚናገራቸውና በሌላ በኩል ደግሞ እንዳልተቀበልን የሚናገራቸው ነገሮች ምን ምንድናቸው? የጢሞቲዎስን ሁኔታ አስመልክቶ ጳውሎስ ይህንን ለምን መናገር የፈለገ ይመስልሃል? በራስህ ህይወትስ ይህንን እውነት በሥራ መተርጎም የምትችልበት ሁኔታ ታያለህ ወይ?
5. ቁ8-10 ላይ በእምነት ልጁ ለሆነው ለጢሞቲዎስ የሚያስተላልፈው ምክር ምን የሚል ነው? ቁ9-10 ላይ የሰፈረው ሃሳብ ከጢሞቲዎስ ለወንጌል መከራ መቀበልና በወንጌል ካለማፈር ጋራ ሊገናኝ የሚችለው በምን መንገድ ነው?
6. በቁ11-12 ላይ ጳውሎስ ተሾምኩ ብሎ የሚናገራቸው ሶስት ነገሮች ምን ምንድናቸው? ከዚህ ክፍል እንደምንረዳው ይህ ሰው ከእግዚአብሄር የተቀበለውን ሹመት በሥራ ላይ ለማዋል መትጋቱ ያተረፈለት ነገር ምንድነው ትላለህ? እንደሹመቱ በመኖሩ ምክንያት ከመጣበት መከራ ባሻገር ጳውሎስ የሚያየው አንድ ነገር ምንድነው? አንተስ የምታተኩረው ዛሬ በምታልፍበት መከራ ላይ ይሆን ወይስ ጌታህ ሲገለጥ የምታገኘውን ክብር?
7. ቁ13-14 ላይ ሐዋርያው ጢሞቲዎስን የሚያዘው ሁለት ነገሮች ምንና ምንድናቸው? ‹በቁ14 ላይ ‹የተሰጠህን መልካሙን አደራ›› ሲል የሚናገረው ስለየትኛው አደራ ነው? ይህ ዓደራስ ስለሚጠበቅበት ሁኔታ ጳውሎስ ምን ይናገራል?
8. በቁ15-18 ላይ ስንመለከት ከሐዋርያው ጋራ በአገልግሎት ከጸኑትና ከተውት በቁጥር ማንኛቸው ይበልጣሉ? ጢሞቲዎስ የትኞቹን እንዲመስል ነው የሚያበረታታው? ጳውሎስም እንደሌሎቹ የተቀበለውን አደራ ጥሎ ዘወር እንዳይል ያደረገው ነገር ምንድነው ትላለህ? እኛ አይናችንን የምንጥልባቸው በዙሪያችን ባሉት የተቀበሉትን አደራ ጥለው በሚኮበልሉት ላይ ሳይሆን ታማኝና አደራ ጠባቂ በሆነው በጌታ ላይ ሊሆን ይገባዋል፡፡

# ጥናት ሁለት 2ኛ ጢሞ 2፡1-13

የጥናት ዓላማ፡- የእግዚአብሄርን ቃል እንድንረዳና ውስጣችን ሰርጾ ገብቶ ሥራውን እንዲሰራ ካስፈለገ፤ እኛ ራሳችን ሳንቻኮል ጊዜ በመውሰድ ማሰላሰል (meditate) እንደሚገባን ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹እኔ የምለውን ልብ በል፤ ጌታ በሁሉም ነገር ማስተዋልን ይሰጥሃልና፡፡›› 2 ጢሞ 2፡7

1. 2ኛ ጢሞ 2፡1-13 በአንድነት ይነበብ። በቁ1 ላይ ጢሞቲዎስ እንዲያደርግ የሚነገረው ነገር ምንድነው? በቁ2 ላይስ ሌላ እንዲያደርግ የተሰጠው መመሪያ ምንድነው? የእነዚህ ሁለት ትዕዛዞች ቅደም ተከተል ምን ለእኛ ምን ያስተምረናል?
2. ቁ2 ላይ ለምንድነው ጳውሎስ ‹‹ከእኔ የሰማኸውን›› በማለት ነገሩን በማጥበብ መናገር ያስፈለገው? ከዚህ ከጳውሎስ አነጋገር የምትማረው ነገር ካለ ለወገኖች አካፍል።
3. በቁ3-4 ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ ክርስትናን ከምን ጋራ በማነጻጸር ነው ሲናገር የምናየው? ከዚህ ክፍል አነጋገር ስንመለከት ከወታደር የሚጠበቀው አንድ ነገር ምንድነው? በ2ኛ ቆሮ 5፡9 ላይ ሐዋርያው የሚናገረውንና በዚህ በቁ4 ላይ የተጻፈውን በማንበብ ስለራሳችን ህይወት ልንማር የምንችለው ነገር ምንድነው?
4. ቁ5 ላይ ደግሞ ጳውሎስ ክርስትናን ከሌላ ነገር ጋራ በማነጻጸር ሲናገር እናያለን፤ ምንን ነው ከክርስትና ጋራ ሲነጻጸር የምንመለከተው? በዚህ ውድድር ውስጥ ከሚሳተፈው ሰው ስለሚጠበቅበት ነገር የሚናገረው ሃሳብ ምንድነው?
5. በቁ3-6 ላይ ሐዋርያው ስለወታደር፣ ስፖርተኛና ስለገበሬ ያሰፈራቸው ምሳሌዎች እያንዳንዳቸው የክርስትናን ህይወት በምን መንገድ ማየት እንድንችል ይረዱናል ትላለህ?
6. በቁ8-9 መሰረት የጳውሎስ ወንጌል ሆኖ የተነገረው ነገር ምንድነው? ሐዋርያው መከራን ለመቀበሉና ለመታሰሩ ምክንያት አድርጎ የሚናገረው ነገር ምንድነው? በዚህ ክፍል ውስጥ ‹‹የእግዚአብሄር ቃል ግን አይታሰርም›› ብሎ ሲናገር ምን ለማለት ፈልጎ ይመስልሃል?
7. በቁ10-13 መሰረት ጳውሎስ በመከራ የሚጸናው ለምን ብሎ ነው? እግዚአብሄር የመረጣቸው ስለሆኑ እሱ በፈለገው መንገድ ያድናቸዋልና እኔ መከራ መቀበል አያስፈልገኝም አለማለቱ ለእኛ የሚያስተምረን ነገር ምንድነው?
8. ከቁ3-6 ስለወታደር፣ ስፖርተኛና፣ ስለገበሬ ከነገረው በኋላ በቁ7 ላይ ጢሞቲዎስን እንዲያደርግ የመከረው ነገር ምን ነበረ? እንደ ጳውሎስ አነጋገር ከጌታ ማስተዋልን ለመቀበል የሰዎች ሃላፊነት ምንድነው? አንተስ ጌታ በቃሉ የሚናገርህን ነገር ልብ ብለህ ለማሰላሰል ጊዜ ትወስዳለህ ወይ? መንፈስ ቅዱስ በቃሉ የሚናገረውን መረዳት ከፈለግን በእርጋታ ጊዜ ወስደንና ልብ ብለን ማንበብ አስፈላጊ ነገር መሆኑን ልንረዳ ያስፈልገናል።

# ጥናት ሶስት 2ኛ ጢሞ 2፡14-26

የጥናት ዓላማ፡- እንደ እግዚአብሄር አገልጋዮች ሃሳባችንንና ትምህርታችንን የሚቃወሙትን ሰዎች በየዋህነት በማቅናት ወደ እውነት እንዲደርሱና ከተያዙበት ነገር የምናስመልጥበትን እንጂ በክርክር የምናሸንፍበትን መንገድ ፈላጊዎች መሆን እንደሌለብን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹የጌታ አገልጋይ…እውነትን ወደ ማወቅ ይደርሱ ዘንድ፣ እግዚአብሄር ንስሃን እንደሚሰጣቸው ተስፋ በማድረግ የሚቃወሙትን በየዋህነት የሚያቀና መሆን ይኖርበታል፤ ይኸውም…ከዲያቢሎስ ወጥመድ ያመልጣሉ በማለት ነው፡፡›› 2ኛ ጢሞ 2፡24-26

1. 2ኛ ጢሞ 2፡14-26 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ14 ላይ ጢሞቲዎስ የኤፌሶንን አማኞች እንዲያስጠነቅቅ የተነገረው ነገር ምንድነው? ለምንድነው ጳውሎስ ይህ አይነቱን ማስጠንቀቂያ አስፈላጊ ሆኖ ያገኘው?
2. በቁ14-17 አነጋገር መሰረት፤ ከንቱ ልፍለፋና በቃላት መነታረክ በለፍላፊው ሰው ህይወት፣ በሰሚዎች ህይወትና በሌሎች በዙሪያው ባሉት ሰዎች ህይወት ሊያስከትል የሚችላቸውን ሶስት ዓይነት ውጤቶ ተናገር፡፡ ከጌታ የሚያርቅ፣ ሎችን የሚያፈርስና፣ አካባቢን እንደቁስል የሚበክለው ከንቱ ልፍለፋ በአንተስ ህይወት ምን ያህል ሥፍራ ተሰጥቶታል?
3. በቁ15 ላይ ጢሞቲዎስ ምን እንዲያደርግ ነው ሐዋርያው የሚያበረታታው? በዚህ ቀጥር ውስጥ ሃዋርያው ጳውሎስ ለጢሞቲዎስ የሰጠውን ትዕዛዝ፤ ከላይ በጥያቄ ተራ ቁጥር ሁለት ላይ ከተጠቀሱት ዓይነት ሰዎች ጋራ በማነጻጸር ተናገር፡፡
4. ቁ17-19 ‹ከእነዚህም መካከል ሄሜኔዎስና ፊሊጦስ ይገኛሉ›› ለምንድነው ጳውሎስ የሰዎችን ስም በግልጽ እየጠራ መናገር ያስፈለገው? በነዚህ ቁጥሮች በተለይም በቁ19 ላይ የጌታን ስም ለሚጠሩ ሰዎች መመሪያ ሆኖ የተነገረው ነገር ምንድነው? የዚህን መመሪያ እውነተኛነት ለማረጋገጥ ጳውሎስ የተጠቀመበት አነጋገር ምን የሚል ነው?
5. በቁ20-21 ላይ ጳውሎስ ትልቅ ቤት በማለት የሚናገረው ስለምን ይመስልሃል? ከአውደ ጥናቱ ጋራ በማገናዘብ ስናነበው፤ ብርና ወርቅ፣ እንዲሁም ደግሞ እንጨትና ሸክላ ተደርገው ሊታዩ የሚችሉ ምሳሌዎች የሚታይህ ከሆነ ተናገር፡፡
6. ሐዋርያው ጳውሎስ በቁ22-23 ውስጥ ጢሞቲዎስ እንዲያደርግ የሚያበረታታው ሶስት አስፈላጊ ነገሮች ምን ምንድናቸው? ሐዋርያው ሃጥያትን መሸሽ ብቻ ሳይሆን ጽድቅን ደግሞ መከታተል አስፈላጊ ሆኖ ያገኘበት ምክንያት ለምንድነው ብለህ ታምናለህ? አንተስ ከሃጥያት ከመሸሽ አልፈህ ጽድቅንም ትከታተላለህ ወይ?
7. በቁ24 ላይ ስናነብ ስለጌታ አገልጋይ ማንነት የተሰጡት መግለጫዎችን አንድ በአንድ በመዘርዘር ተናገር፡፡ ‹‹የጌታ አገልጋይ ሊጣላ አይገባውም›› የሚለውን አነጋገር በሃዋርያው ጳውሎስ ህይወት ላይ ተፈጻሚ ሆኖ የምናየው በምን መንገድ ነው?
8. ቁ25-26 የጌታ አገልጋይ በተለይም በሚቃወሙትና ሃሳቡን በማይደግፉት ሰዎች ፊት ሊያሳየው ስለሚገባው ባህርይ ምን እናነባለን? ይህንን እንዲያደርግ የሚጠበቅበት ምክንያትስ ለምንድነው? አንተስ ሃሳብህን ለማይደግፉና ለሚነቅፉህ ሰዎች ምላሽህ ምን ይመስላል? ጳውሎስ ተቃዋሚዎቹን ለማቅናት በተለያየ መንገድ እንደሚሞክር ሁሉ፤ እኛም የሚቃወሙንን ለማጥፋት ሳይሆን ህይወታቸውን ለመቀየር የምንጥር ሰዎች ልንሆን ይገባናል፡፡

# <u>ጥናት አራት 2ኛ ጢሞ 3፡1-17</u>

የጥናት ዓላማ፡- በየጊዜው የምንማራቸው ብዙ ነገሮች እንዳሉ የታወቀ ቢሆንም፤ አጥብቀን ልንይዛቸው የሚገቡንና በሥራ ላይ እንድናውላቸው የሚጠበቅብን ነገሮች ከትምህትት አልፈው ውስጣችን የገቡና የተረዳናቸው ማለትም (convinced) የሆንባቸውን ብቻ እንደሆነ ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹አንተ ግን በተማርከውና በተረዳኸው ጽና፤ ይህንን ከማን እንደተማርከው ታውቃለህና‹‹ 2ኛ ጢሞ 3፡14

1. 2ኛ ጢሞ 3፡1-16 በአንድነት ይነበብ፡፡ ይህ ክፍል ሲጀምር፤ ጳውሎስ ለጢሞቲዎስ ልብ እንዲል የሚያስጠነቅቀው ነገር ምንድነው? በቁ1-5 ላይ የተዘረዘሩት 19 ለሚሆኑት ነገሮች በአንደኛነት ደረጃ መሪ ሆኖ የተቀመጠው ምንድነው?
2. በቁ1-5 ላይ ተዘርዝረው በምናነባቸው ነገሮች መሃል ቢያንስ ሶስት ጊዜ የተነገረ አንድ ቃል ምንድነው? ሶስቱን ነገሮች ስታነብና አካባቢህ ን ስትመለከት እነዚህ ነገሮች ምን ያህል ሥፍራ ተሰጥቷቸው ታያለህ? እነዚህን አስመልክቶ የአንተስ ህይወት ምን ይመስላል?
3. ማቴ 22፡39ንና የመሳሰሉትን ክፍሎች ስናይ ባልንጀራችንን እንደራሳችን እንድንወድ ይነግረናል፤ ታዲያ በዚህ ክፍል ለምንድነው ራስን መውደድ እንደ ክፉ ነገር ሆኖ የቀረበው? እዚህ ላይ የተዘረዘሩት ነገሮች በህይወታቸው የሚከሰቱት ሰዎች እግዚአብሄር የለም ባይ ከሃዲዎች ናቸው ወይስ ምን ዓይነት ሰዎች ናቸው ብለህ ታምናለህ?
4. በቁ4-5 ላይ ‹‹ከእግዚአብሄር ይልቅ ተድላን የሚወዱ›› የሚለው አነጋገር ምን ማለት እንደሆነ ነው የምትረዳው? በነዚሁ ቁጥሮች ውስጥ ሃይማኖታዊ መልክ ይዞ ሃይሉን መካድ ሲል ምን እንደሚገባህ አስረዳ፡፡
5. ቁ1-5 ስለ ሰዎቹ ማንነትና ባህርይ የሚናገር ነው ቢባል፤ በቁ6-9 የሰፈረውን ሃሳብስ ምን የሚናገር ነው ማለት እንችላለን? በቁ6-9 ላይ እነዚህ ሰዎች ያደርጋሉ በማለት ጸሐፊው የሚነግረን ነገር ምንድነው? በቁ8 ላይ ጳውሎስ የእነዚህን ሰዎች ማንነት የሚገልጥባቸው ሶስት መጠሪያዎች ምን ምንድናቸው?
6. ‹‹አንተ ግን›› በማለት ጳውሎስ ለጢሞቲዎስ በቁ10 ላይ የሚናገረው ከማን ጋራ እያነጻጸረ ነው? በአካባቢው የሚያየው ሰው ሁሉ የሚኖረው በቁ1-9 የሚመስለውን ዓይነት ህይወት ሊሆን እንደሚችል አሳስቦት፤ ለምን ይመስልሃል በቁ10-12 ላይ ጳውሎስ የራሱን ህይወት ሊያስታውሰው የፈለገው? ቁ12 ላይ ያለውን የጳውሎስ አነጋገር እንዴት እንደምትረዳው ለወገኖች ተናገር፡፡
7. ቁ15-17ትን ስናነብ የእግዚአብሄር ቃል በውስጡ ምን እንዳለበት ነው የሚነግረን? የእግዚአብሄርን ቃል ልንጠቀምባቸው የምንችላቸው ምን ምን መንገዶችን ታያለህ? እነዚህን ሁሉ የመጠቀማችን ግቡ ምን እንደሆነ ነው የምናየው? ቃሉን ስትጠቀምበት ሰዎችን ለበጎ ሥራ ለማብቃት እንደሆነ ምን ያህል ታስባለህ?
8. ወደላይ መለስ ብለን ቁ14ትን ስናይ ‹‹አንተ ግን›› በማለት በቁ13 ካሉት ሰዎች ጋራ ሲያነጻጽረው ይታያል፡፡ የእነዚህን ሰዎች ህይወትና ጳውሎስ በጢሞቲዎስ ህይወት እንዲታይ የሚመክረውን ነገሮች ተናገር፡፡ ‹‹አንተ ግን በተማርከውና በተረዳኸው ጽና›› ሲል ጢሞቲዎስ በተማረው ነገር ሁሉ እንዲጸና ነው ወይ የሚያዘው? ካልሆነስን ለመጽናቱ ተጨማሪ የሚያስፈልገው ነገር ምን ታያለህ?
9. በህይወትህ ምን ዓይነት ነገሮችን ነው አጥብቀህ ልትይዛቸውና ልትኖርባቸው የምትጥረው? የምንማራቸው ብዙ ነገሮች እንዳሉ የታወቀ ቢሆንም፤ በሥራ ላይ እንድናውል የሚጠበቅብን ከትምህትት አልፈው ውስጣችን የገቡና የተረዳናቸው (convinced) የሆንባቸውን ብቻ መሆኑን ልንረዳ ያስፈልገናል፡፡

# ጥናት አምስት 2ኛ ጢሞ 4፡1-22

*የጥናት ዓላማ፡- በአጠገባችን ተገኝተው ይረዱናል ወይም ያግዙናል ብለን የተማመንባቸው ሰዎች ባይደርሱልን፤ እነርሱን ከመቀየምና በእነርሱ ከማዘን ይልቅ፤ ሰዎችን በመላክም ሆነ በተለያየ መንገድ ደርሶ የሚረዳንን እግዚአብሄርን ማመስገን ለመማር፡፡*

*የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹በተከሰስኩበት ነገር ማንም ሊያግዘኝ አልመጣም…ጌታ በአጠገቤ ቆሞ አበረታኝ፣ ከአንበሳም መንጋጋ አዳነኝ፡፡ ጌታ ከክፉ ነገር ሁሉ ያድነኛል››* 2ኛ ጢሞ 4፡16-17

1. 2ኛ ጢሞ 4፡1-22 በአንድነት ይነበብ፡፡ ምዕራፍ አራትን ስናነብ ጳውሎስ ለጢሞቲዎስ የሰጠው ትዕዛዝ ጥብቅና ትኩረት እንዲሰጠው መገለጉን የሚያሳየን ነገር የትኛው?
2. በቁ2 በስተመጨረሻ ላይ ጳውሎስ ለጢሞቲዎስ የሚመክረውን ምክር በ2ኛ ጢሞ 3፡16 ላይ ስለቃሉ ከተነገረው ጋራ በማየት፤ የጳውሎስን ምክር በሁለት ቃላት ብቻ ጠቅልለህ ተናገር ብትባል ምን ትላለህ? ከጳውሎስ አነጋገር ጢሞቲዎስ ቃሉን መጠቀም የሚኖርበት ምክንያት ለምንድነው?
3. በቁ3-5 ላይ ትክክለኛውን የእግዚአብሄር ቃል ለመቀበል የማይወዱ ሰዎች ባህርያትና የሚያደርጓቸው በዚህ ክፍል ተዘርዝረው የምናያቸውን ነገሮች ተናገር፡፡ በአንጻሩ ጢሞቲዎስ እንዲያደርግ የታዘዛቸው አራት ነገሮች ምን ምንድናቸው? በዚህ ሥፍራ ሐዋርያው የተናገራቸው ዓይነት ተማሪዎችም ሆነ አስተማሪዎች በዚህ ዘመን ገጥመውህ ያውቃል ወይ? የአንተስ ህይወት የጢሞቲዎስን ወይስ የሌሎቹን ሰዎች ህይወት ይመስላል?
4. በቁ6-7 ላይ ስናነብ ጳውሎስ በህይወቱ በቅርብ እንደሚሆን የተገነዘበው ነገር ምንድነው? በነዚህ ሁለት ቁጥሮች ጳውሎስ ህይወቱን መለስ ብሎ ሲያይና አሁን ያለበትን በማሰብ ጢሞቲዎስ እንዲያውቅለትና እንዲገነዘብ የሚፈልጋቸው ቢያንስ አራት ነገሮችን ተናገር፡፡
5. ጳውሎስ ከፊት ለፊቱ ያለውን ዘመን ሲያስብ ቁ8 ላይ ከሚናገረው አነጋገር ጨልሞበት ነው ወይስ ብሩህ ሆኖ እንደሚታየው ነው የሚናገረው? ስለዚህ ጊዜ የሚናገራቸውን ነገሮች ሁሉ በመዘርዘር ተናገር፡፡ ጳውሎስ ብሩህ ሆኖ የሚያየው ነገር ጢሞቲዎስንም እንደሚጨምር የምናየው እንዴት ነው? አንተስ የህይወትህን ፍጻሜ ስታስብ ብሩህ ሆኖ ታየዋለህ ወይ?
6. ቁ9-13ትን ስናነብ ጢሞቲዎስ እንዲያደርግ የታዘዛቸው ሶስት ነገሮች ምን ምንድናቸው? ማርቆስ የተባለው ሰው በሐዋ ሥራ 15፡38-40 ጳውሎስ ጠቃሚ ሰው እንዳልሆነ ወስኖ ነበረ፤ ማርቆስን ጠቃሚ ሰው ሆኖ እንዲገኝ የረዳው ሰው ማነው ብለህ ታምናለህ? ለምን ይህንን ማለት እንደቻልክ አስረዳ፡፡
7. ‹‹ጌታ ግን የእጁን ይሰጠዋል›› እግዚአብሄር ዋጋውን እንደሚከፍለው ካመነ በቁ14 ላይ ጳውሎስ ለምንድነው ስለ አንጥረኛው እስክንድሮስ ለጢሞቲዎስ መንገር ያስፈለገው?
8. ጥሮፊሞስ ስለተባለው ሰው በቁ19-22 ባሉት ቁጥሮች ውስጥ ጸሐፊው የነገረን ነገር ምንድነው? ጳውሎስ ይህ ሰው እንዲፈወስ ሳይጸልይለት እንደማይቀር ይታወቃል፤ ታዲያ ለምን ይመስልሃል ጸልዮለት ፈውሱን ተቀብሎ ወደ አገልግሎቱ መሰማራት ያልቻለው?
9. ቁ16-22ትን መለስ ብለን ስናይ ጳውሎስ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ራሱን ባገኘበት ሰዓት ከእኔ ጋራ ይቆማ ብሎ ያሰባቸው ጓደኞቹን በምን ሁኔታ ነው ያገኛቸው? እግዚአብሄርንስ በምን ሁኔታ ነው የተለማመደው? ሰዎችን ስትፈልግ እግዚአብሄር የደረሰልህ ጊዜ አለወይ? ሰዎች ይደርሱልኛል ብሎ ልብን በሰዎች ላይ ከማድረግ ይልቅ፤ በእግዚአብሄር ላይ መተማመንና እርሱን ተስፋ ማድረግ እንደሚሻል ልትረዳ ያስፈልግሃል፡፡